# <u>የዚያ ትውልድ ፈርጦች</u>

(አንሙት፣ ከለንደን፣ 22 ሚያዝያ 1998)

ገዳይን እናውግዝ፣ ግድያ እንዲያበቃ፣
ታሪክን አናጉድፍ፣ አንቀባ ጭቃ።

የዚያ ትውልድ ፈርጦች፣ ህያው የሚያበሩ፣
ኮከብ የነበሩ፣ ሆነው የሚኖሩ፣
ዘር ሳይገድባቸው፣ ከየጎጥ መንደሩ፣
በወል ተሰባስበው፣ ህብር የፈጠሩ፣
ሩቅ ግባቸውን፣ ህልም እንደቋጠሩ፣
መትረየስ አጭዷቸው፣ የትም የተዘሩ፣
የአንድነት ገድላቸው፣ ይውጣ ይዘከሩ!

የዚያ ትውልድ ፈርጦች! አዎ ይዘከሩ!
አሙተዋል ሞትን፣ ሞተው እንዳይኖሩ፣
አጥንታቸው ብእር፣
ቀለሙ ደማቸው፣
ያረፉበት አፈር፣
ሆኖ ብራናቸው፣
ገድለው የወደቁት፣
ሞትን በሞታቸው፣
የፃፉት በተግባር፣
ክቡሩ ገድላቸው፣
ይነገር! ይዘከር፣
ትውልድ ይወቃቸው፣

አዎ!
የትውልድ ፈርጦችን፣ ማህፀኗ ያፈራ፣
የትንታጎቹ እናት፣ ውሉዋቸው ሲወራ፣
አርአያ ሆነውን፣ ፋናቸው ሲያበራ፣
ገፁዋ ፈካ ይበል፣ በልጁዋ ትኩራራ፣
እንጅ ለምን ትክሰል፣ ባዘን ተኮማትራ፣
እንደ ፈራሽ አካል፣ ታሪኩንም ቀብራ?!
ሀቅን አረም ውጦት፣ ውሸት አይዘራ!

ቁዋንቁዋ ሳይዛቸው፣ ዘር ጎሳ ሳይቆጥሩ፣
በኢትዮጵያዊነት፣ በአንድ እየዘመሩ፣
በወል አላማ ስር፣ ታሪክ እየሰሩ፣
ፉሽስት ጨፍጭፎዋቸው፣ የትም የተዘሩ፣
የዚያ ትውልድ ፈርጦች፣ ዛሬም ይዘከሩ!

የዚያ ትውልድ ገድል፣ በሀሰተኞች ጋድ፣ ታስሮ ተሸብቦ፣
ከኡግ ነጭ ወተት፣ በውሸት ውሸት ታልቦ፣
ከምንም ምንምን አጉል ተመግቦ፣
ቀትረ ቢስ እንዳይሆን፣ እንዳያዲግ ይሄ ትውልድ፣ እየፋፋ ጠግቦ፣
ይውጣ ታሪካቸው፣ ይያዝ ተመዝግቦ።

«ነፍሴን ውሰዱ እንጅ! እምነቴ አይሙት!» ባለ፣
ለሀቁ ደም ዋጋ፣ ህይወት በከፈለ፣
ሞት በሞት አሙቶ፣ ስለተገደለ!?

ገዳይ ሟች ወንጅሎ፣ ግልብጥ እያበለ፣
እውነት አይኮነን፣ ውሸት ተወድሶ፣
የዚያ ትውልድ ፈርጦች፣ ታሪክ ተድበስብሶ!
ይነገር ገድላቸው፣
ይውጣ ታሪካቸው፣
የደም እዳ አለበት፣ ሀገር ይወቃቸው።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.